# የኑሮ መሻሻሉ እውነታ ሲፈተሽ!

ከሃብሮማይ
ghabrom@yahoo.com

ምክንያታዊነት የሚገለፀው ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተህ አመዛዝነህ እንጂ በስሜት በመነዳትና ጥቂቶችን ለማስደት ብዙዎችን በመጉዳት እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ አንድ አገር ዕድገት አስመዝግባለች ወይስ አላስመዘገበችም ብሎ ለመናገር ብዙ መስፈርቶች አሉ፡፡ ሁሉም አገሮች ለማደግ ይጥራሉ ግን ስለጣሩ ብቻ የተመኙትን ዕድገት ማስመዝገብ አይችሉም፡፡ በመጀመሪያ ማድረግ ካለባቸው ነገር ዋነኛው ከአገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚሄድ ፖሊሲና ስትራተጂ መቅረፅ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሬት ላይ ያለውን ነገር በኢኮኖሚ ንድፈ ሃሳብ መተርጎም ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሌላ አነጋገር ምክንያታዊ መሆን ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ በህዝብ ብዛቷ በአፍሪካ ሶስተኛ ደረጃ ይዛለች፡፡ የስነ ምጣኔ ሃብት አቀንቃኞች ስለ ህዝብ ብዛትና ያለው ፋይዳ ሲተነትኑ በሁለት መንገድ ነው የሚገልፁት፡፡ አንደኛው የህዝብ ብዛት እንደ መጥፎና የድህነት አንድ ገፅታ አድርገው ነው የሚያስቡት፡፡ እሱም ያለህን የህዝብ ጉልበት በአግባቡ ሳትጠቀም ስትቀርና የውስን ህዝብ ገቢ ለህዝቡ ሲካፈል ከሚያመጣው ፋይዳ አንጻር ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የህዝብ ብዛት እንደ ሃብት ምንጭ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ህዝቡ ባለው አቅምና ጉልበት ከተረባረበ ለአገሪቷ ዕድገት ትልቅ አስተዋፆ ስለሚያበረክት፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት ስርዓታት የነዚህን የኢኮኖሚ ቀመር ታሳቢ ሳታደርግና ምክንያታዊ ያልሆነ አካሄድ ትከተል ስለነበር የገዢዎቹን ስልጣን ማራዘሚያ ታሳቢ ያደረገ ፖሊሲ እየቀረጸች በመሄዷ የነበራትን ሃብት በአግባቡ ባለመጠቀምዋ ለረሃብና ለእርስ በርስ ግጭት ተጋላጭ ሆና እንደቆየች የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ ለዚህም ነው ባለፉት ስርዓታት የአገሪቷ የህዝብ ብዛት የድህነት ምንጭ ተደርጎ ሲወሰድ የነበረው፡፡

በአገሪቷ ምርታማ ዜጋ ተብሎ ይጠራ የነበረው ጥቂት በከተማ የሚኖር ህዝብ ነበር፡፡ እሱም ስራ ፈጥሮ የራሱ የሆነ ስራ የሚሰራ ሳይሆን በወቅቱ በነበሩ ጥቂት ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራና ገቢውም እዚህ ግባ የማይባል ነበር ፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ ገቢ የነዚህ ጥቂት ሰዎች ገቢ ነው የነበረው፡፡ ከ 84% በላይ የሆነው ህዝብ በሚኖርበት የገጠሩ አካባቢ ግን ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ አልነበረውም፡፡ በዚህ ምክንያት የያንዳንዱ ዜጋ የነፍስ ወከፍ ገቢ በኢኮኖሚክስ ስሌት የአገሪቱ ገቢ ሲካፈል በአገሪቱ ህዝብ ስለሚሆን ውጤቱ በጣም ዝቅተኛ ነበር፡፡

የደርግ ስርዓት ከተገረሰሰ በኋላ መንግስት የአገሪቷን ተጨባጭ ሁኔታ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ከኢኮኖሚክስ ንድፈ ሃሳብ ጋር በመቃኘት ምን ሃብት አለን? ምንስ ያጥረናል? የሚለውን ጉዳይ በጥልቀት ከመረመረ በኋላ ስራ ላይ ሊውል የሚችል ሰፊ ጉልበት፣ የካፒታል እጥረት እንዲሁም በከተማ የመሬት እጥረት፣ በቆላ የአርብቶ አደር አከባቢ ግን ሰፊ መሬት እንዳለን በጥናት አረጋገጠ፡፡

የኢኮኖሚክስ ንድፈ ሃሳብ በበኩሉ ያለህን ሃብት አሟጠህ መጠቀም እንዳለብህ ይገልፃል፡፡ በአገራችን ያለ ሃብት ደግሞ ጉልበት ስለሆነ ጉልበትን በስፋት መጠቀም የሚያስችል ፖሊሲ ተቀርፆ ወደ ተግባር ተሸጋገረ፡፡

ጉልበት በስፋት ያለው በገጠር አከባቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ከ 84% በላይ የሚሆነው ህዝብ በገጠር ስለሚኖር፡፡ በመሆኑም ጉልበትን በስፋት እንጠቀማለን ከተባለ ገጠርን ማእከል ያደረገ ፖሊሲ መቅረፅ ግድ ነው የሚሆነው፡፡ እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለብን ነገር አሁን ያለው መንግስት መጀመሪያ ሲነሳም

የህዝብን ጥያቄ ይዞ ስለተነሳ መመለስ የነበረበት የማንንም ፍላጎት ሳይሆን የህዝብን ፍላጎት ብቻ ነው፡፡ መሆንም ያለበት ይኼው ነው፡፡

በአገራችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ገጠርን ማእከል አድርጎ ፖሊሲ መቅረፅ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነበር፡፡ ህዝቡም ተጠቃሚ የሚሆነው በዚህ ስለሆነና ህዝቡም የሚፈልገው ይሄንኑ ስለሆነ መንግስት ገጠርን ማእከል ያደረገ ስትራቴጂን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ይህንንም የመረጠው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ "ሱስ" ስላለው ወይም የሌሎች ንድፈ ሃሳቦች "ጥላቻ "ስላለው ሳይሆን ለአገሪቱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ ምክንያታዊ መሆን ያስፈልጋልና፡፡

ጉልበትን በስፋት መጠቀም ከተፈለገ ያለውን የሰው ሃይል በዕውቀት፣ በክህሎት ማዳበርን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ስራዎችን መስራት ያስፈልግ ነበር፡፡ የጤና ፖሊሲ ከመቅረፅ ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት ማስፋፋትና ሌሎችም፡፡

አገሪቷ ያላትን ሃብት በብቃትና አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለመጠቀም በቅድሚያ የሰው ሃይሏ ጤናማ መሆን አለበት፡፡ ካለባት የካፒታል እጥረት አኳያ ለያንዳንዱ ህብረተሰብ የሕክምና ወጪ ለማውጣት አቅሙ ስለሌላት የመከላከል ፖሊሲ ተቀርፆ በያንዳንዱ ቀበሌ የጤና ኤክስቴንሽን ተስፋፍቷል፡፡ ከመከላከሉ ባሻገር የሚታመም ሰው ስለሚኖር ለ25ሺ ሰዎች አንድ ጤና ጣቢያ በመገንባት ውጤታማ የሆነ ስራ ተሰርቷል፡፡ በመከላከል ብቻ አፍሪካ ከሚያጠቋት በሽታዎች 85%ቱን መከላከል እንደሚቻል የ WHO መግለጫ ያመለክታል፡፡

በትምህርት ዘርፍም ከመጀመሪያ ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በብዛት ተገንብተዋል፡፡ አሁንም እየተገነቡ ነው፡፡ ሰባት ዓመት የደረሰ ሕፃን ወደ ትምህርት ቤት መግባት አለበት የሚል ግብ ተቀምጦ ዕድሜው የደረሰ ሕፃን ወደ ትምህርት ቤት በማስገባት በኩል ሰፊና ውጤታማ ስራ ተሰርቷል፡፡ በጎልማሶች ትምህርትም እንደዚሁ፡፡

በመሆኑም  በተቀረፀው የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ህዝቡ በብዛት መሳተፍ ብቻ ሳይሆን የልማት ተቋዳሽም መሆን ጀምሯል፡፡ አገሪቷ ግብርና መር ስትራቴጂ በመከተሏ በገጠር ያለውን ጉልበት በሰፊው መጠቀም ተችሏል፡፡ ጤንነቱ የተጠበቀ  አቅም እያዳበረ ያለ ልማታዊ ሃይል በብዛት እየተፈጠረ ይገኛል፡፡

ለዚህም ነው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በመምህራን ማህበር ስብሰባ ላይ "መንገድ ቢገነባ ይፈርሳል፤ እንዴ ተገንብቶ የማይፈርስ ግን የሰው ሃይል ነው" ያሉት፡፡ አሁን ባለው የአገሪቷ ተጨባጥ ሁኔታ የህዝብ ብዛት እንደ ሃብት (asset) እንጂ እንደ ዕዳ (liability) መታየት ቀርቷል፡፡

አገራዊ ገቢያችንም የጥቂቶች ገቢ ድምር ሳይሆን የአብዛኛው ህዝብ ገቢ ድምር ውጤት መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ ህዝብ በተረባረበበት ጥረት የሚገኘው ገቢ ለራሱ ለህዝቡ ሲካፈል የያንዳንዱ ዜጋ ገቢ ከፍ እያለ እንደሚሄድ አያጠያይቅም፡፡

ይህ ማለት ግን ሁሉም ዜጎች እኩል ገቢ ይከፋፈላሉ ማለት እንዳልሆነ እሙን ነው፡፡ ማንኛውም ዜጋ በሰራው ስራ መጠን ተጠቃሚ ይሆናል ማለት እንጂ! ይህም በመሆኑ ነው የአገራችን  አርሶ አደሮች በሰሩት ስራ መጠን እኩል ተጠቃሚ እየሆኑ የሚገኙትና ኑሯቸውንም በከፍተኛ ደረጃ  እያሻሻሉ ያሉት፡፡ በከተማም የሚኖሩ ማህበረሰብም በጥቃቅንና አነስተኛ ስራዎች ተደራጅተው ኑሯቸውን እያሻሻሉ የሚገኙት፡፡

ህዝቡ አሁን ካለበት ዓቅምና ክህሎት በላይ ሲጨምር ደግሞ የኢትዮጵያ ተስፋ ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መገመት አይከብድም፡፡ ምክንያቱም ህዝቡ ዓቅሙ እየተገነባና ክህሎት እየተላበሰ በሄደ ቁጥር ምርታማነቱ እየጨመረ ይሄዳል፣ በዛም ልክ ገቢውን ይጨምራል፣ ገቢውን ከጨመረ የመግዛት ዓቅሙ መጨመሩ አይቀርም፡፡

የመግዛት ዓቅማቸን ሲጨምር የአገራችን የገበያ ስፋት (market area) ይጨምራል፡፡ በኢኮኖሚክስ ስሌት የገበያ ስፋት /ጥበት የሚለካው የአገሪቷ ህዝብ ብዛት በህዝቦቿ የመግዛት ዓቅም ሲባዛ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከላይ እንደገለፅኩት ዕውቀትና ክህሎት እያዳበረ የሚገኝ ምርታማ ማህበረሰብ እየተፈጠረ ነው ያለው፡፡ በዚሁ ምክንያትም የአገሪቷ ገበያ እየሰፋ መጥቷል፡፡ ገበያው በመስፋቱ ደግሞ ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የነፃ ኢኮኖሚ ተከታይ በመሆኗ በግብርናም በኢንዱስትሪ ውጤቶችም ከግሎባላይዜሽን ጋር የሚሄድና በዓለም ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል ገበያ ተኮር አመራረትን በመከተልና በውጪ ተፈላጊ ምርቶችን በማምረት ረገድ ጠንክራ በመስራት ላይ ነች፡፡ ይህ ለአገሪቷ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመሆን ተጠናክሮ እየተሰራበት ያለ ነገር ነው፡፡

የአገሪቷ ጠቅላላ ዓመታዊ ምርት (Gross Domestic Product) ከላይ በገለፅኳቸው ምክንያቶች የተነሳ እየጨመረ በመሄድ ላይ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ GDP ማለት በአንድ ዓመት ውስጥ የአንድ አገር ገቢ ሲቀነስ የውጭ ኢንቨስትመንት ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አገሪቷ ግብርናን ማእከል ያደረገ ፖሊሲ መከተሏና የግብርና ውጤቶችን እንደ ግብአት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋቷ እየጠቀማት ይገኛል፡፡

አገሪቷ የተረጋጋችና ሰላም የሰፈነባት በመሆኗም የግል ባለሃብቶች በከፍተኛ ደረጃ መዋእለ ንዋያቸውን እያፈሰሱ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ነው የአገሪቱ GDP ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል የሚባለው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የአገሪቷ ኢኮኖሚ አስተማማኝ በሆነ መንገድ እያደገ መሆኑን ነው የሚያሳየው፡፡ ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል፣ የፍጆታ መጠን (consumption) ጨምሯል፣ የመንግስት ወጪ (government

spending) ጨምሯል፡፡ ጠቅላላ ዓመታዊ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ማለት፣ የተለያዩ የመንግስት ወጪዎች፣ ኢንቨስትመንት እንዲሁም ወደ ውጭ የምታስወጣውና የምታስገባው ልዩነት (net export) ድምር ነው፡፡ ለዚህም ነው የኢትዮጵያ GDP ጨምሯል የሚባለው፡፡

ዓመታዊ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ከጨመረ ለምን የያንዳንዱ ዜጋ የኑሮ ደረጃ አይሻሻልም ? የ GDP መጨመር የኑሮ ደረጃን "የግድ" ያሻሽላል የሚል አስተሳሰብ ያላቸው ጥቂቶች አይደሉም፡፡

GDP ከጨመረ የኑሮ ደረጃ "የግድ" መጨመር አለበት መባሉን ኢኮኖሚስቶቹ አይቀበሉትም፡፡ ነገር ግን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል GDP አንዱና ዋነኛ መለኪያ መሆኑን ይስማሙበታል፡፡ አገራዊ ገቢ (national income) አንዱ መለኪያ ነውና፡፡

GDP ከጨመረ የኑሮ ደረጃ መሻሻሉ የግድ ነው የማይባልበት ዋነኛው ምክንያት GDP በአገር ውስጥ የሚካሄዱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ብቻ እንጂ በአገር ውስጥ የሚካሄዱትን የውጭ ኢንቨስትመንቶች ስለማይለካ ነው፡፡ በመሆኑም GDP መጨመሩ የግድ የኑሮ ደረጃ ያሻሽላል የሚል አስተሳሰብ የለም፡፡

ለምሳሌ አንድ አገር 100% ምርቷ ወደ ውጭ የምትልክ ከሆነችና ነገር ግን ምንም ወደ አገር ውስጥ የምታስገባው ምርት ከሌለ በመለኪያው መሰረት ከፍተኛ GDP ነው የምታስመዘግበው፡፡ ስለዚህ የGDP መጨመር የኑሮ ደረጃን "የግድ" ያሻሽላል የሚል አስተሳሰብ ስህተት ነው፡፡ የኑሮ ደረጃን ለማሻሻል ግን የ GDP መጨመር ግድ ይላል፡፡ ለዚህም ነው GDP ለኑሮ ደረጃ መማሻሻል ቀጥተኛ መለኪያ አይደለም የሚባለው፡፡ እንደ Background Information on GDP and GDP Deflator መፅሐፍ ገለፃ፡፡

ኢትዮጵያ ለተከታታይ ስድስት ዓመታት ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግባለች፡፡ ይህን መሰሉ ዕድገት ከዚህ በፊት በፍፁም እንዳልነበረ

ቢታወቅም ከሰማይ የመጣ ዕድገት ግን አይደለም፡፡ **ነፃነት ያለውና** በአገሪቷ ተጨባጭና ምክንያታዊ የሆነ ፖሊሲና ስትራተጂ በመቅረጿና ፖሊሲውም "በወረቀት ብቻ ተፅፎ እንዳይቀር" በተግባር ለመተርጎም መላው ህዝቡ ንቅናቄ በፈጠረና ባሳተፈ መልኩ በመረባረቡ እንጂ፡፡

ኢትዮጵያን በአሉታዊ ገፅታ ብቻ ሲፈርጃት የኖረው ታዋቂው "ዘኢኮኖሚስት" መፅሔት ኢትዮጵያ በምታስመዘግበው ምጣኔ ሃብታዊ ዕድገት በመደነቅ በአልማዝና ነዳጅ የተፈጥሮ ሃብት ከበለፀጉ አገሮች ተርታ ልትሰለፍ መሆኗን መግለፁ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር የ 2009 አጠቃላይ የኢኮኖሚ ትንበያ መሰረት አገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ዕድገት ከሚያስመዘግቡ አስር አገሮች መካከል አንዷ እንደምትሆን ነው ይሄ መፅሔት የገለፀው፡፡ ከአገሮቹ መካከልም ከኳታር፣ አንጎላና ማላዊ ቀጥሎ ቻይናን አስከትላ አራተኛ ደረጃ ትይዛለች ብሎ ነው ዘግቦ የነበረው፡፡ ይህ የሚያሳየው የአገሪቷ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተማማኝ በሆነ መልኩ እየሄደ መሆኑን ነው፡፡ እንደሚታወቀው ዘኢኮኖሚስት መፅሔት አብዛኛውን ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ብዙም የሚጠቅም ነገር አውርቶ አያውቅም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ እየጎላና ለመሸፋፈን የማያመች ሁኔታ ሲፈጠር ሃቁን ማውጣቱ የሚያስገርም አይደለም፡፡ ዋናው ቁምነገር የአገራችን ኢኮኖሚ በአስተማማኝ መንገድ እያደገ መሆኑ ነውና!

ሰሞኑን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም ባወጣው ሪፖርት ላይ ኢትዮጵያ በሰው ሃብት ልማት ጠቋሚ (human development index) መሰረት ዕድገት እያስመዘገበች መሆኗን ጠቁሟል፡፡ የሰው ሃብት ልማት ጠቋሚ (HDI) ማለት ሰዎች ጤናማና ረጅም ህይወት መኖራቸውን የሚያረጋግጥ፣ የትምህርት መስፋፋት፣ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ወዘተ የሚያጠቃልል መለኪያ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ መለኪያ አገሮች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ ያደጉ፣ ታዳጊና ያላደጉ አገሮች ተብለው የሚፈረጁትም በዚሁ መለኪያ መሰረት ነው፡፡

በዚህ ሪፖርት ላይ ኢትዮጵያ በሰው ሃብት ልማት እኤአ ከ 1995-2007 የሰው ሃብት ልማቷ በዓመት 3.13% አድጎ ነበር፡፡ አሁን ግን ከነበረው 0.308 ዓመታዊ ዕድገት ወደ 0.414 ዓመታዊ ዕድገት ከፍ ብሏል፡፡ ይህ ማለት የ 0.106 ብልጫ አሳይቷል ማለት ነው እንደ ተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ሪፖርት፡፡

የሰው ልማት ማለት ከአገሪቱ ገቢ ከፍ ማለትና ዝቅ ከማለት በላይ የሚታይ ትልቅ የሰው ሃብት መጠቆምያ (Index) ነው፡፡ ለህብረተሰቡ ምቹ የሆነ ሁኔታ መፍጠርና ህዝቡም ዓቅሙን አሟጦ የሚያመርትበት እንዲሁም ህዝቡ በፍላጎቱ የሚኖርበት ሁኔታ መፍጠር ማለትም እንደሆነ የሰው ሃብት ልማት ሪፖርትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያዘጋጀው ታዋቂው ፓኪስታናዊ ኢኮኖሚስት ማህቡብ አል ሃቅ ይገልፃል፡፡

በመሆኑም ኢትዮጵያ ባሳየችው ተከታታይና ፈጣን ዕድገት ህዝቡ ተጠቃሚ እንደሆነ ነው የሚያሳየን፡፡ እንደሚታወቀው የአገሪቷ የኢኮኖሚ ዕድገት ከሌሎች የኢኮኖሚ ዕድገት ለየት የሚያደርገው ዕድገቷ ሰብአዊ ዕድገት መሆኑ ነው፡፡ ይህ ማለት በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የመንገድ፣ የትምህርት፣ የጤና … ወዘተ ልማት ስራዎች ሁሉም ዜጎች እኩል የሚጠቀሙባቸው በመሆናቸውና ሃብታምና ደሃ የማይለያዩ መሆናቸው ነው፡፡

ለዚህም ነው ረጅም መንገድ ተጉዘው ሲማሩ የነበሩ ህፃናት አሁን በደጃቸው ትምህርት ቤት ተከፍቶላቸው እየተማሩ ያሉት፣ እናቶች በወሊድ ጊዜ በጤና ጣቢያ ርቀት ምክንያት ለሞት የሚዳረጉበትን ዘመን አብቅቶ አሁን በየቀበሌው ጤና ኬላ ተገንብቶላቸው ህይወታቸውን ለመታደግ የበቁት፡፡ የአገሪቷ ህዝብ በተገኘው ፈጣንና ተከታታይ ልማት በሰራው ስራ መጠን ተጠቃሚ በመሆኑ የኑሮ ደረጃውን ማሻሻል ጀምሯል፡፡ይህ ደግሞ የህዝቡ አማካይ የዕድሜ ዘመን (life expectancy) እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል፡፡ አርሶ አደሮች በተገነባው መንገድ ምርታቸውን በቀላሉ ወደ ገበያ ማቅረብ ችለዋል፡፡ ስለሆነም የአገሪቷ ህዝብ ኑሮ

እንደተሻሻለ ይህ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራምም በሪፖርቱ ላይ ይህን ነው ያለን፡፡

በኢትዮጵያ በአንዳንድ ቦታዎች ዘንድሮ የዝናብ እጥረት ቢያጋጥምም በአጠቃላይ ሲታይ ግን ጥሩ የሆነ ዝናብ ዘንቧል ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው የአገሪቷ ክፍሎች ጥሩ የሆነ ዝናብ የነበረ ሲሆን በአንዳንድ ቦታዎች ግን ዝናቡ የተፈለገውን ያህል አጥጋቢ አልነበረም፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን ስፋት ባላቸው አከባቢዎች ላይ ጥሩ የሆነ ዝናብ ስለዘነበ ከፍተኛ ምርት ይመረታል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ የምርቱ መጠን የዝናብ እጥረት ላጋጠማቸው አንዳንድ ቦታዎችም የሚተርፍ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ስለሆነም በዝናብ እጥረት ምክንያት ለክፉ የሚዳርጉ ሁኔታዎች የሉም፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንድ ተንታኞች በተለመደው ፖለቲካዊ ማህበራዊና ርእዮተ ዓለማዊ ቅኝታቸው አማካኝነት በኢትዮጵያ በዝናብ እጥረት ሳቢያ ከ 12 ሚልዮን በላይ ህዝብ ሊራብ ይችላል እያሉን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ካለው የአገሪቷ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይጣጣምና ከሃቅ የራቀ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ አጭር ጊዜ እንኳ ጥሩ የሆነ ዝናብ ዘንቧል፡፡ ይሁን እንጂ ተንታኞቹ የተለመደው ከሃቅ የራቀ መረጃቸው እያስተጋቡልን ነው፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም ሰሞኑን ባወጣው ሪፖርት ላይ የህዝባችን አማካይ የዕድሜ መጠን በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩን ጠቁሟል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ህዝብ የዘርፈ ብዙ መሰረታዊ ልማቶች ተጠቃሚ እየሆነ መምጣቱን የሚያሳይ ተጨባጭ ሐቅ ነው፡፡ ህዝቡ በሰራው ስራ መጠን ተጠቃሚ እየሆነና ኑሮውን እያሻሻለ በመሄድ ላይ መሆኑ በራሱ ለተሻለ ልማትና ዕድገት የሚያበቃው እየሆነ እንደሚሄድ ጥርጥር የለውም፡፡ ለዚህም ነው መንግስትና ህዝብ የጀመሩትን የልማት ጥረት አጠናክረው መቀጠል አለባቸው የምለው፡፡ ሰላም!